ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
ሰሜን አሜሪካ ጽ/ቤት
Kinijit for Unity and Democracy Party (Kinijit)
North America Office

# ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ኮሚቴ ግንቦት 8 ( May 16) የጠራውን ህዝባዊ የተቃውሞ የፖለቲካ ሰልፍ የሚመለከት የቀረበ ማብራርያ

የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም አገር ወዳድ ለሆናቹህ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቅንጅት የግንቦት 8 ( May 16) ሰላማዊ ሰልፍን አስመልክቶ ሀላፊነት በተሰማው መንገድ በማካሄድ ላይ መሆኑን እየገለጸ ከዚህ ውጭ በዚህ ጉዳይ በቅንጅትና በቅንጅት አመራር ዙርያ የሚሰነዘሩ ጤናማ ያልሆኑ አስተያየቶች፤ እንዲሁም የፖለቲካ ጠቀሜታ ወይም ቅንጅትን ጠልፎ ለመጣል ፍላጎት ያላቸው፤ ይህንኑ የታሰሩ መሪዎቻችንን ከማንቋሸሽ ጀምሮ በተደጋጋሚ ያካሄዱ አካሎች የሚያናፍሱትን አሉባልታ፤ ለህዝብ ዳኝነት የምንተዋቸው እንጂ በእጃችን ያሉትን አብይ ሀገራዊ ጉዳዮች በማግለል በዚህ ጉዳይ እሰጥ አገባ ውስጥ እንደማንገባ በአክብሮት እንገልፃለን።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ በህዋስነቱ:-

- የቅንጅት መሰረታዊ እምነት የግለሰብን ነፃነት ሀሳቡንም በተግባር የመተርጎም መብት የቀበላል፤
- ግንቦት 7 ( May 15) የኢትዮጵያ ህዝብ ኢህአዴግን በድምፅ ጥሎ ተስፋ የጣለበትን ቅንጅትን መምረጡን፤ ማንም በምንም ሊቀይረው የማይችል መሆኑን ያምናል፤
- በተለያየ የዓለምና የአሜሪካ ከተሞች ያሉ የቅንጅት አባላት ደጋፊዎችና የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦት 7ና (May 15) በአከባቢው ባሉ ቀናቶች፤ በተለያየ መንገድ ስሜቱን ይገልጻል፤ይህንንም ከልብ ይደግፋል፤
- እንደ መሪ ፓርቲነቱ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብሎ በህዋስ ደረጃ ያመነበትን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመውሰድ መብት አለው።

ከነዚህ ነጥቦች በመነሳት የሚከተሉት እርምጃዎች ተወስደዋል።

1. በጥር (January) መጀመርያ በተካሄደው የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ጉባዔ በግንቦቱ ምርጫና ከምርቻው ጋር በተያያዘ በተከሰቱ ሁኔታዎች ዙርያ ሊወሰዱ ይገባቸዋል ብሎ ካመነባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱና ዋናው ህዝባዊ የፖለቲካ ሰልፍ ማድረግ ነው። ይህም በዜና ማሰራጫዎች ተገልጧል።
2. ይን መመርያ በመከተል በጥር (January ) መጀመርያ አከባቢ የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት አመራር በፖለቲካ ኮሚቴው አማካኝነት የቀረበለትን የሰላማዊ ሰልፍ ዝርዝር አፀደቀ። ይኸውም:-
    ሀ. ሰላማዊ ሰልፍ በዋናነት ሥሥት መልክ ይኖረዋል 1. የድጋፍ 2. የመታሰቢያ ወይም መግለጫ 3. የተቃውሞ
    ከዚህ በመነሳት በወቅቱ በሀገራችን የተከሰተውን ሁኔታ በመገምገም፤ በተለይም የኢትዮጵያ ህዝብ ምም ይሁን ምን ስሜቱን ለመግለፅ እንዳይችል መታፈኑን በመገንዘብ፤ ሊደረግ የሚገባው የተቃውሞ የፖለቲካ ሰልፍ እንዲሆን ወሰነ።
    ለ. የተቃውሞው መሰረት የግንቦት 7 (May 15) ምርጫን አስመልክቶ በኦፊሴልና በተግባር አጠቃላ አፈና የተጀመረበትና አሁንም የቀጠለበት

ተግባሩ የተጀመረበት ግንቦት 8 ( May 16) እንዲሆን ይም ሰልፍ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. በመካሄድ በአሜሪካን የኮንግረስ ፅ/ቤት እንዲጠናቀቅ፤ ብዙ የኮንግረስ አባላት በማክሰኞ ቀን ስለሚገኙ፤ ይህም ከአከባቢው ሁኔታ የቀኑ አመራረጥ አመቺ መሆኑና፤ በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ የፖለቲካ ጠቀሜታ ስላለው በተጠቀሰው ቀን የተቃውሞ የፖለቲካ ሰልፍ እንዲካሄድ እንቅስቃሴው እንዲጀመር ተወሰነ:: በሌሎች አከባቢዎች እንደየአከባቢው ሁኔታ በተሌየ መንገድ እንዲካሄድና ለዚህም የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ድጋፍ እንደሚሰጥ ተወሰነ::

3. በዚሁ በጥር ( January) መጀመርያ በጽ/ቤቱ በኩል ፈቃድ ለመጠየቅ የሚያስፈልጉ ፎርሞች ተሞልተው ለፈቃድ ሰጭዎች ክፍል ገቢ ተደረገ::
4. በየካቲት 7 (February 14) የፈቃድ ሰጭ ክፍል 6 የተለያዩ የፈቃድ ሰጭ አካላት ባሉበት የመጀመርያ ውይይት ተካሄደ፤ ከዚያም የሚቀጥለው ቀጠሮ ለሚያዝያ 10 (April 18) እንዲሆን ተወሰነ::
5. በየካቲት ( March ) አጋማሽ ጀምሮ ለተለያዩ የዜና ማሰራጫዎችና በየአከባቢው ላሉ የድጋፍ ኮሚቴዎች የተቃውሞ የፖለቲካ ሰልፍ በዋሽንግተን እንደሚካሄድ በኦፊሴል ተገለፀ
6. በየሳምንቱ በየራዲኖችና በየስብሰባው ይኸው ሲሰራጭ ሰነበተ::
7. በሚያዝያ 6 ( April 14 ) ዓርብ ቀን ምሽት በግንቦት 7 ( May 15) ስለሚደረግ ሰልፍ ጉዳይ ለመወያየት በማግስቱ ቅዳሜ ሚያዝያ 7 ( April 15) ከምሽቱ 12 ሰዓት (6:00PM) ስብሰባ እንድንገኝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ከህብረቱ በኢሜል ደረሰ::
8. በማግስቱ ሚያዝያ 7 (April 15) የህብረቱ መሪ ለሆኑ ግለሰብ ስልክ በመደወል የግንቦት 8 (May 16) ዕቅድ ከነምክንያቱ ቀደም ሲል በዜና ማሰራጫ መነገሩን አስረዳን:: ይህም ሆኖ፤ በስብሰባው ለመገኘት እንደምንችል ገለፅን::
9. ሆኖም በሌላ ተደራራቢ ስብሰባ ምክንት ባለመቻሉ፤ ይኸው በስልክ ተገለፀ::
10. ሚያዝያ 8 (April 16) ቅንጅት ባካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ የሰላማዊ ሰልፍ ጉዳይ ተነስቶ ለምን በግንቦት 8 ( May 16) እንደሚደረግ በቂ ማብራርያ ተሰጠበት:: ከህዝቡም ሙሉ ነሙሉ ተቀባይነትን አገኘ::
11. በተከታታይ በራዲዮ ማስታወቅያና ማብራርያ ቀጠለ::
12. ሚያዝያ 8 (April 16) ቀን ከህብረቱ የበላይ ሀላፊ ጋር ረዘም ያለ ውይይት ተካሄደ፤ በዚህም ቅንጅት ይህ የፖለቲካ ሰልፍ መሆኑን እንደሚያምን የቀኑ መረጣ የፖለቲካ ጠቀሜታ እንዳለው ጥሪውን በጋራ ለመጥራት ፈቃደኛ መሆናችንን ገልጸን፤ መልስ እንደምናገኝ ተነገረን::
13. ሚያዝያ 10 ( April 18) ከፈቃድ ሰጭ አካላቶች ጋር የጋራ ስብሰባ ተካሂዶ የፕሮግራሙ የመጨረሻ ስምምነት ተደረገ:: በስብሰባው መጨረሻ ላይ ሚያዝያ 9 (April 17) በኛ በኩል በግንቦት 8 (May 16) አይነት ጥያቄ በሜይ 15 ሰልፍ ለማካሄድ የሚፈልግ ሌላ ቡድን በግለሰብ አማካኝነት መጠየቁ ተነገረን::
14. ከህብረቱ መሪ ጋር በድጋሚ ተነጋግረን ሶስት ተወካዮች እንደሚላኩልንና በጋራ ተወያይቶ ለመቀጠል ተስማማን
15. ሶስት የሕብረት ተወካዮች ባሉበት ሚያዝያ 12 (April 20) ሰፋ ያለ ውይይት አካሂደን ለሰልፍ ዝግጅት አብረዋቸው እየተሰበሰቡ ያሉ ሌሎች አካላት መኖራቸውን በመግለፅ ተለይቶ ለመቀጠል እንደሚከብዳቸው ገለፁ:: በኛ በኩል እነሱ ከተስማሙ ከሌሎቹም ጋር ጭምር ቢሆን ለመቀጠል ፈቃደኝነታችንን ጠቀስን:: እስከ አሁን መልስ አላገኘንም::

በመጨረሻም ቅንጅት በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ የመረተው በመሆኑ፤ በዚህም የህዝብ አመኔታ የተጣለበት በመሆኑ፤ መሪዎቹ በሙሉ የታሰሩበት በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ የወቅቱ የፖለቲካ እምብር የቅንጅት ጉዳይ በመሆኑ፤ ቅንጅት በአጠቃላይና፤ ቅንጅት በተለያየ የህዋስ ደረጃ ለህዝብ የትግል ስልትና የፖለቲካ አቅጣጫ የመጠቆም የሕሊና

ስልጣን (Moral Authority) ያለው ፓርቲ ነው፡፡ ይህ የህዝብ የሆነ ፓርቲ በወሰነው መሰረት ግንቦት 8 (May 16) በሚደረገው የተቃውሞ የፖለቲካ ሰልፍ በመካፈል ለወገኖቻችን አለኝታ እንድንሆናቸው በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን፡፡

766 Rock Creeck Church Road NW, Washington DC 20010
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: kinijitUSA@kinijit.org